# በደቡብ ብ/ብ/ህ/ክ/መንግሥት

# የአቅም ግንባታ ቢሮ

## የ2000 ዓ/ም ዕቅድ

ሐምሌ 1999
አዋሳ

# መግቢያ

የክልላችን ህዝብ ከሚገኝበት ኋላ ቀርነትና የድህነት ህይወት እንዲላቀቅ ባለፊት ተከታታይ ሶስት ዓመታት ያስመዘገብናቸው የልማት ውጤቶች ዛላቂ እንዲሆኑና ቀጣይነት እንዲኖራቸው በክልሉ የሚታዩ ውስብስብ የማስፈጸም አቅም ችግሮች የሚፈቱበትና መልካም አስተዳደር የሚሰፍንበት ሁኔታ ማመቻቸት ያስፈልጋል ። ይህንንም ዓላማ ከግብ ለማድረስ የአምስት ዓመት የማስፈጸም አቅም ግንባታ ስትራቴጂና ዕቅድና የ2000 ሴክቶሪያል ዕቅድ ያዘጋጀ ሲሆን ከዚሁ ዕቅድ ካስኬድ በማድረግ የ2000 ዓ/ም የቢሮው ዕቅድ ተዘጋጅቷል ።

የቢሮው የ2000 ዓ/ም ዕቅድ ሲዘጋጅ ባለፉት ዓመታት ያከናወናቸውን ተግባራትና ያጋጠሙትን ችግሮች በመገምገም በ1999 በጀት ዓመት በየደረጃው የታዩትን ችግሮች ደረጃ በደረጃ በመፍታት የሴክተሩን ግቦች እውን ማድረግ ያስፈልጋል ። በዚሁ መሠረት ያልተማከለ አስተዳደርን ማጠናከር ፣ በየደረጃው የማስፈጸም አቅም ግንዛቤ ሥራ መሥራት ፣ የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች የሚፈቱበትን ስልት መቀየስና የሪፎርም ሥራዎችን በተጠናከረ መልኩ ለመተግበር የሚያስችል የማስፈጸምና የመፈጸም አቅም በየደረጃው መገንባት ቁልፍ ሥራችን ይሆናል ።

በመሆኑም የዘመኑ ዕቅድ በክልሉ በሚገኙ ሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች ዲሞክራሲና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የማስፈጸም አቅም ግንባታ ፕሮግራሞችን በተቀናጀ ሁኔታ ማከናወን ቅድሚያ ትኩረት የተሰጠው ነው። ከዚህ አንጻር የቢሮው ዕቅድ በዘርፎች ፣ በመምሪያዎችና በሥራ ክፍሎች እስከ ሠራተኛው ድረስ በየደረጃው ተዘርዝሮ ውጤት ተኮር የአፈጻጸም መርህን ተከትሎ የሚተገበር ነው ። ከዚህ በመነሳት የዕቅድ ዘመኑ የአቅም ግንባታ ሥራችን ዓላማ ፣ ቁልፍ ፣ አበይት፣ ንዑሳን ተግባራትና ዓመታዊ ግቦች እንደ ሴክተር በጥቅልና በየፕሮግራሞች በተናጠል እንደሚከተለው ተዘርዝር ታቅዷል።

## 1. ቁልፍ ተግባር

የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞችን ቀጣይነትና ዘላቂነት ባለው ሁኔታ ለመተግበር የተፈጠረ ቅንጅታዊ የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም

## 2. ዓመታዊ ግቦች

2.1 በ3ቱ የሪፎርም አስቀጣይ አስፈጻሚና ተቋማት ፣ በ13 ዞኖች ፣ 134 ወረዳናዎችና 22 የከተማ አስተዳደሮች የአቅም ግንባታ የሥራ ክፍሎች የተፈጠረ የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም፣

2.2 በተመረጡ 7 ሴክተር መ/ቤቶች የተተገበረ መሠረታዊ የአሰራር ስርዓት ለውጥ፣

2.3 የተዘረጋ የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች ትግበራ ስርዓት ፣

2.4 ለክልሉ የፍትህ ሥርዓት ስኬታማነት የተፈጠረ ተቋማዊ አቅም ፣

2.5 ሥራ ላይ የዋሉ የመልካም አስተዳደር ፓኬጅ አዋጆችና መመሪያዎች ፣

2.6 ሥራ ላይ የዋሉ የተቋማት አሰራርና አደረጃጀት ደንብና መመሪያዎች ፣

2.7 የመረጃ ስርዓት የተዘረጋላቸው 10 የክልል መ/ቤቶች፣ 104 የወረዳዎችና 300 ቀበሌዎች ፣

## 3. ዓላማ

የአቅም ግንባታ ፖሊሲ ስትራቴጂና ፕሮግራሞችን አተገባበር ቀጣይነት ለማፋጠን የሚያግዝ የማስፈጸም አቅም መገንባት ፣

3.1 የሲ/ሰ/ማ/ፐ/ንዑስ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶችን በሁሉም የአስተዳደር እርከን ተግባራዊ ማድረግ ፣ ድጋፍ ፣ ክትትልና ሥልጠና መስጠት ፣

3.2 የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶችን በሁሉም የአስተዳደር እርከኖች ተግባራዊ ማድረግ ፣ ድጋፍና ስልጠና መስጠት ፣

3.3 የወረዳ አቅም ግንባታ ፕሮግራምን በማጠናከር የገጠር ወረዳና ቀበሌ መልካ አስተዳደር ፓኬጅን በተሟላ ሁኔታ መተግበር ፣ መከታተል፣ መደገፍና ስልጠና መስጠት ፣

3.4 የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴጅኖሎጂን በየደረጃው ባሉ የአስተዳደር እርከኖች ተግባራዊ ማድረግ ፣ ድጋፍ መስጠት፣ መከታተልና ማስልጠን፣

3.5 የኢንጂነሪንግ አቅም ግንባታ ፕሮግራም በፈጻሚ ተቋማት ተግባራዊ መደረጉን መከታተል ፣ መደገፍ ማስልጠንና ተቋማዊ መሠረቱን ማጠናከር ፣

## 4. <u>በዓመቱ የሚጠበቁ ውጤቶች</u>

4.1 በ3ቱ የሪፎርም አስፈጻሚና አስቀጣይ ተቋማት ፣ በ13 ዞኖች ፣ 134 ወረዳዎች በ22 ከተማ አቅም አስተዳደር ግንባታ የሥራ ክፍሎች የተፈጠረ የማስፈጸም አቅም፣

- አደረጃጀታቸውንና አሰራራቸውን የለውጡ 3 የሪፎርም አስፈጻሚና አስቀጣይ ተቋማት (አቅም ግንባታ ቢሮ ፣ ሲ/ሰ/ኤጀንሲና የክልሉ ሥራ አመራር ተቋም) ፣ 13 ዞኖች ፣ 134 ወረዳዎችና 22 የከተማ አስተዳደር አቅም ግንባታ ተቋማትና መ/ቤቶች፣

- በመገልገያ መሳሪያዎች የተጠናከሩ 80% የክልል ፣ የዞን ፣ የወረዳና የከተማ አቅም ግንባታ መ/ቤቶች፣

## 4.2 በተመረጡ 7 ሴክተር መ/ቤቶች የተፈጠረ መሰረታዊ የአሰራር ሥርዓት ለውጥ፣

- የተጠናቀቀ ፣ የመሠረታዊ የአሰራር ሥርዓት ለውጥ ማኑዋል ፣
- መሰረታዊ የአሰራር ሥርዓት ለውጥ ስልጠና የወሰዱ የክልል ግብረሀይል አባላት፣
- ስልጠና የወሰዱ የ7 መ/ቤቶች የመሰረታዊ የአሰራር ሥርዓት ለውጥ ቡድን አባላት ፣
- መሰረታዊ የአሰራር ሥርዓት ለውጥ ለሚተገበሩ 7 መ/ቤቶች የተሰጠ ቴክኒካል ድጋፍ ፣
- መሰረታዊ የአሰራር ሥርዓት ለውጥ ትግበራ ያጠናቀቁ 7 መ/ቤቶች፣

### 4.3 የተዘረጋ ለተቀናጀ የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች ትግበራ የተዘረጋ ሥርዓት

- የውጤት ተኮር ሥርዓት እንዲተገበር ድጋፋዊ ክትትል የተደረገባቸው 80% የክልል ፣ የዞን ፣ የወረዳና ከተማ መ/ቤቶች ፣
- በተቀናጀ ሁኔታ በተዘረጋ ሥርዓት የተተገበረ የሲ/ሰ/ማ/ፕሮግራም ፣
- አምስቱን የሲ/ሰ/ማ/ፕ በተቀናጀ ሁኔታ በመተግበርና ራሳቸውን በመለወጥ የተቀላጠፈ አገልግሎት መስጠት የቻሉ መ/ቤቶች ፣

## 4.4 ለክልሉ የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም ስኬታማነት የተፈጠረ ተቋማዊ አቅም ፣

- በተቀናከ ሁኔታ በተዘረጋ ሥርዓት የተተገበረ ፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም፣

- የተቋቋመና ሥራ የጀመረ ፣ የፍትህ አካላት ባሙያዎች ማሰልጠኛ ማዕከል፣
- 400 ስልጠና የጀመሩ አዳዲስ ዕጩ የወረዳ ዳኞችና ዐቃቤያነ ህጎች፣
- በልማት ኂላ ቀር ከሆኑ ወረዳዎች ተመልምለው በዲፕሎማ የህግ ትምህርት የጀመሩ 150 ሰልጣኞች፣
- ኮሚኒቲ ፖሊሲንግን ለመምራትና ለመተግበር የተደራጀ ኮር ቡድን፣
- ስልጠና ላይ ለሚገኙ ዕጩ የወረዳ ዳኞችና ዐቃቢያነ ህጎች የተደረገ ክትትልና ቴክኒክ ድጋፍ፣
- ታትመውና ተጠርዘው የተሰራጩ በክልል የወጡ አዋጆችና ደንቦች፣

## 4.5 ሥራ ላይ የዋሉ የመልካም አስተዳደር ፓኬጅ አዋጆች መመሪያዎችና ተግባራት ፣

- ተግባር ላይ የዋሉ 8 አዋጆችና መመሪያዎች፣
- በሁሉም የአስተዳደር እርከኖች በተሟላ ሁኔታ የተተገበረ የመልካም አስተዳደር ፖኬጅ፣
- ከፌዴራል አቅም ግንባታ ሚ/ር ጋር በመተባበር የተዘጋጀ የአርብቶ አደር አካባቢ የመልካም አስተዳደር ፓኬጅ፣
- የወረዳ ተቋማትን አደረጃጀትና አሰራር ለማሻሻል የተዘጋጁ 5 ማኑዋሎች፣ መመሪያዎችና የፖሊሲ ሰነዶች ፣
- በሥራ ላይ የዋሉ 2 አዋጆችና 1 ያልተማከለ የአካባቢ አስተዳደር ፖሊሲ ፣

- ተግባር ላይ የዋለ ፣ የወረዳ ተቋማት ዝቅተኛ የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃና የክትትል ሥርዓት ማኑዋል፣

- የተጠናቀቀ 1 ክልላዊ የወረዳ የሰው ሃይል ልማት ስትራቴጂ የሥልጠና ፍላጎትና የስልጠና ፖሊሲ ሰነድ ፣

**4.6 በክልሉ በሁሉም የአስተዳደር እርከኖች ለኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀም የተዘረጋ ሥርዓት፡-**

- የመረጃ ሥርዓት የተዘረጋላቸው 10 የክልል መ/ቤቶችና 104 ወረዳዎች፣

- በመረጃ ማስተላለፍ ሥራ የሰለጠኑ 250 የዞንና የወረዳ የኢኮቴ ባለሙያዎች፣

- በመሠረታዊ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም የሰለጠኑ 2000 የዞንና የወረዳ መ/ቤቶች ባለሙያዎችና ኃላፊዎች ፣

- የተቋቋሙና አገልግሎት መስጠት የጀመሩ 6 የማህበረሰብ መረጃ ማዕከላት ፣

- በ34 አዲስ ወረዳዎች የተቋቋመ የመረጃ ማዕከላት (Information Centers)

- የተጠናቀቀና ወደ ተግባር የተሸጋገረ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ሥርዓት መመሪያ ፣

- የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ መሣሪያዎች አጠቃቀም የተዘጋጀና ተግባራዊ የተደረገ 1 መመሪያ ፣

- በአጠቃቀም መመሪያው ላይ ለ13 ዞንና 104 ወረዳዎች ለተውጣጡ ባሙያዎች የተሰጠ ስልጠና፣

- ለ13 ዞንና ለ134 ወረዳዎች የተሰጠ የኢኮቴ የቴክኒክ ድጋፍና የጥገና አገልግሎት፣

- ለኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ዝርጋታ የተመረጡ 300 ቀበሌዎች ፣

- ለቀበሌዎች ተገዝተው የተተከሉ 300 ኮምፒውተሮችና አክሰሰሪዎች፣

- ስልጠና የወሰዱ 300 የቀበሌ የመረጃ ሠራተኞች ፣

- ዘመናዊ መረጃ መጠቀም የጀመሩ 300 ቀበሌዎች ፣

## 4.7 የተቀናጀ አቅም ግንባታ ፕሮግራሞች አፈጻጸም ዕቅድ ዝግጅት ሥርዓት፣

- የተጠናቀቀ 1 የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች የአፈጻጸም ዕቅድ ሥርዓት ማኑዋልና መመሪያ ፣

- ለአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች ዕቅድ ዝግጅት ባለሙያዎች የተሰጠ ስልጠና ፣

## 4.8 በአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች አፈጻጸም በክልል፣ በዞን፣ በወረዳና ከተማ የተካሄደ ድጋፋዊ ክትትልና ግምገማ፣

- የተጠናቀቀ 1 የድጋፋዊ ክትትል ሥርዓት ማኑዋልና መመሪያ ፣

- 4 ጊዜ የተካሄደ የተቀናጀ የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች አፈጻጸም ድጋፋዊ ክትትል ፣

- የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች አፈጻጸም ባመጣው ፋይዳ ላይ የተካሄደ 1 ጥናት፣

4.9 **የፀረ ኤች. አይ. ቪ. ኤድስ ሥርዓተ ፆታ እንቅስቃሴን በማጠናከር የቫይረሱን ሥርጭት ለመግታትና ሥርዓተ ፆታ ተግባራትን ለመፈጸም የተደረገ ድጋፍና ዕገዛ ፣**

- ለ13 ዞንና ለ134 ወረዳ ሀላፊዎችና ባለሙያዎች በኤች አይቪ ኤድስና ሥርዓተ ፆታ ዙሪያ የተሰጠ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና፣
- የኤች አይቪ ኤድስን ሥርጭት ለመግታት የተደረገ የበጀት ድጋፍ ፣
- በኤች አይቪ ኤድስና ሥርዓተ ፆታ ዙሪያ ተዘጋጅቶ የተሰራጨ የግንዛቤ ማስጨበጫ ብሮሸሮች፣
- በአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች ዕቅድ ዝግጅትና አፈጻጸም የተካተተ የሥርዓተ ጾታ ዕቅድ ፣
- በአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች በሚካሄድ ስልጠና የተሳተፉ 30% ሴቶች፣
- ስለ ሥርዓተ ጾታ ሜንስትሪሚንግ ለ13 ዞንና 134 ወረዳና 22 ከተማ የአቅም ግንባታ ኃላፊዎች የተሰጠ ስልጠና፣

## 5. <u>የቁልፍ ተግባሩ ዝርዝር ተግባራት</u>

### 5.1 ሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም፡-

#### 1. ግብ

በ3ቱ የሪፎርም አስፈጻሚና አስቀጣይ ተቋማት በ13 ዞን፣ 134 ወረዳዎችና 22 የከተማ አስተዳደር አቅም ግንባታ ተቋማትና መ/ቤቶች የተቀናጀ የማስፈጸም አቅም ተፈጥሯል ፡፡

2. **ዓላማ:-**

በየደረጃው የሚገኙ የመንግሥት ተቋማት በራሳቸው ላይ ለውጥ በማምጣት ቀልጣፋና ፈጣን አገልግት እንዲሰጡ ማድረግ ፣

**ዝርዝር ተግባራት :-**

**ሲ/ሰ/ኤጀንሲን በተመለከተ**

- የሲ/ሰ/ኤጀንሲ በራሱ ላይ ለውጥ በማምጣት ተልዕኮውን እንዲወጣ ፣ ድጋፍ ማድረግ ፣ ማሰልጠንና መከታተል ፣
- ኤጀንሲው ተመርጠው የሚሰጡትን መ/ቤቶች በመደገፍና በማብቃት የለውጥ አስቀጣይነት ሚናውን እንዲጫወት መደገፍ ፣
- ኤጀንሲው የሰው ሃይል አስተዳደር ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም ፈጻሚ በመሆኑ በተገቢው መንገድ መፈጸም መቻሉን መከታተል፣ መደገፍና ማብቃለት ፣
- የሥራ አፈጻጸም ምዘናና የጊዜ አጠቃቀም ፕሮጀክትን በተጀመረበት መንገድ እንዲቀጥል የኤጀንሲውን አፈጻጸም መከታተልና መደገፍ፣
- የውጤት ተኮር ዕቅድ አፈጻጸም ምዘና ዘዴ በክልል ፣ በዞንና በወረዳ ደረጃ በሚገኙ በሁሉም የመንግሥት መ/ቤቶች ተግባራዊ እንዲሆን የሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ ተግባሩን በባለቤትነት እንዲመራው ማድረግና መከታተል ፣
- የውጤት ተኮር ዕቅድ አፈጻጸም ምዘና ዜዴ በየወሩ ክትትል እየተደረገና እየተመዘነ የሚሰራ ተግባር መሆኑን እንዲያረጋግጥ ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲን መከታተልና ማብቃት ፣

- በጥርና በሐምሌ ወር የሚደረገው የውጤት ተኮር ምዘና በመርሁ መሠረት መፈጸሙን የሚያሳይ ሪፖርት በሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ እንዲቀርብ በማድረግ አፈጻጸሙን መገምገም፣

- ተመሳሳይ ለሆኑ የሥራ መደቦች ወጥ የሆነ ሞዴል የውጤት ተኮር በኮሚሽኑ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ እንዲሆን መከታተል ፣

- የሰው ሃይል ዕቅድና  የሰው ሃይል ልማት ፕሮጀክቶች ጥናቶች ተጠናቀው ወደተግባር መግባታቸውን መከታተልና ጉድለታቸውን ማረም እንዲቻል ኤጀንሲውን ማብቃት ፣ መገምገምና መከታተል ፣

- አዋጅ ቁጥር 47/1994 በውጤት ተኮር አፈጻጸም ጋር  ተገናዝቦ በአዲስ አዋጅ እንዲተካ ማድረግና ኮሚሽኑ የአዋጁን ይዘት በስፋት እንዲያስተዋውቅ መከታተል ፣ መደገፍ፣

- የሲቪል ሰርቪስ  ኤጀንሲ የBPR ጥናት እንዲጠናቀቅና ወደ ተግባር እንዲገባበት መከታተል ፣ መደገፍና ማብቃት፣

- ከፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ ጋር ትስስር እንዲፈጥርና ጠቃሚ ተሞክሮዎችን አንዲቀስም ማድረግ ፣

- አዲስ ምሩቃን ሥራ ከመጀመራቸው በፊት በተደራጀ ሁኔታ ሞጁል ተዘጋጅቶ ስልጠና እንዲሰጥ ኤጀንሲውን መከታተል ፣ መገምገምና ማብቃት ፣

- ከመልካም አስተዳደር ፓኬጅ ሥራዎች ውስጥ ኤጀንሲውን የሚመለከተውን ለይቶ መተግበር ፣ መከታተልና ማብቃት ፣

## ሥራ አመራር ተቋምን በተመለከተ ፡-

- የሥራ አመራር ተቋም በራሱ ላይ ለውጥ እንዲያመጣ መደገፍ፣ ማስልጠን፣ ማብቃትና መከታተል ፣
- ተቋሙ የለውጥ አስቀጣይ ተግባሩን እንዲወጣ የማያቋርጥ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ፣ ማስልጠን ፣
- ተቋሙ አግባብ ያላቸውን የጥናት ዓነቶች ለይቶ ጥናት እንዲያካሄድ መደገፍ ፣ መከታተል፣
- ተቋሙ የሥልጠና ርዕሶችን ለይቶ በጋራ ሥልጠና መስጠት የሚቻልበትን ሁኔታ ማመቻቸትና መከታተል ፣
- ተቋሙ የምክር አገልግሎት መስጠት የሚችልበትን ሥልት በጋራ ማመቻቸትና አገልግሎቱን መስጠት እንዲጀምር መደገፍ፣ ክትትል ማድረግና ማብቃት ፣
- ተቋሙ ራሱን በለውጥ ሃይል አጠናክሮ ሌሎች ተቋማትን እንዲያበቃ ማድረግ ፣ መደገፍና መከታተል ፣
- ከፌዴራል ሥራ አመራር ኢንስቲትዩት ጋር አብሮ እንዲሰራ ማድረግና ጠቃሚ ልምዶችን በመውሰድ እንዲተገብር መደገፍ ፣ መከታተልና ማጠናከር ፣

## አቅም ግንባታ ቢሮን በተመለከተ

- የሪፎርም አስፈጻሚ የሆነው የአቅም ግንባታ ቢሮ የጀመረውን የ Quick wins ሥራ እንዲያፋጥን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ፣

- በክልል ደረጃ ተመረጡ መ/ቤቶች BPR እንዲያከናውኑ ሥልጠና መስጠት፣ አስተባባሪ ኮሚቴ ፣ Core team እና ልዩ ልዩ ኮሚቴዎችን ማቋቋም መመሪያ ማዘጋጀት ፣ ማሰራጨት ፣ መከታተል ፣ መደገፍ ፣ ማሰልጠንና መተግበር ፣

- ለተመረጡ መ/ቤቶች የBPR ቡድኖች ሥልጠና መስጠት ፣ በበድን ማደራጀትና በየሴክተሩ ማሰማራት ፣ መከታተል ፣ መገምገምና ወቅታዊ እርምት መስጠት ፣

- የተቋቋሙ ቡድኖችን አቅም በተከታታይ ማጎልበት ፣ ማሰልጠንና መከታተል በተገቢው መምራትና ተልዕኮአቸውን እንዲወጡ ማድረግ፣

- አስተባባሪ ኮሚቴውም ሆነ ቡድኖች በዕቅድ እንዲመሩ ሁኔታዎችን ማመቻቸት መከታተልና ማገዝ መደገፍ፣

- በተመረጡ መ/ቤቶች የተጠናው BPR ለውጥ የሚያመጣ መሆኑ በአስተባባሪ ኮሚቴውና በCore team የተመሰከረለት መሆኑን በተገቢው ማረጋገጥና ወደ ተግባር ለመሸጋገር የሚያስችል አደረጃጀት መፍጠር ፣

- የ BPR ጥናት ያጠናቀቁ ተቋማት የተሟላ ውጤት ተኮር ሥርዓት ለመጀመር የሚያስችላቸውን ቅድመ ሁኔታ ማጠናቀቅ ፣

- የ BPR ጥናት በአስተማማኝ ያጠናቀቁ መ/ቤቶች ወደ ተግባር እንዲሸጋገሩ ማድረግ መከታተልና መደገፍ ፣

- በ2001 ዓ/ም BPR ለመጀመር የሚችሉ ተቋማትን መምረጥና ቅድመ ሁኔታ ማመቻቸት ፣

- ዞኖችና ወረዳዎች እንዲሁም BPR ጥናት በአዲስ ያልጀመሩ መ/ቤቶች ቀደም ሲል በጀመሩትና በመሥራት ላይ በሚገኙት የQuick wins

መሠረት እንዲቀጥሉ መከታተል ፣ መመሪያ ማስተላፍና የለውጥ በር እንዲከፍቱ የማብቃት ሥራ ማከናወን፣

- ወረዳዎች የ BPI ጥናት እንዲያከናውኑ መደገፍ መከታተል ፣

- የፈጣን አገልግሎት ማሻሻያ ያስጀመሩ መ/ቤቶችና ተቋማትን መለየት፣ መገምገምና ወደ ተግባር እንዲገቡ ማድረግ ፣ የተሻለ ደረጃ የሚገኙትን ማበረታታት የሚቻልበትን መመዘኛ ማዘጋጀት ፣ የማበረታቻ የሽልማት ሥርዓት መፍጠርና መተግበር ፣

- የክልሉ ሲ/ሰ/ማ/ፕ አስተባባሪ ኮሚቴ ዓመታዊ ዕቅድና መርሃ-ግብር በማዘጋጀት በየወሩ እንዲሰበሰብ በማድረግ ፣ ባጋጠሙ ችግሮች ላይ ወቅታዊ እርምት እንዲደረግ ፣ ችግሮችን በመለየት ለውሳኔ ማቅረብና ተግባራዊ ማድረግ፣
- በBPR ጥናትም ሆነ በፈጣን አገልግሎት ማሻሻያ የተሻለ ውጤት ያላቸውን ሴክተሮች ፣ ዞኖችና ወረዳዎች መምረጥና ክልላዊ ተሞክሮ የሚወሰድበትን የልምድ ልውውጥ አሰራር ሥርዓት ማመቻቸት ፣

- የንዑስ ፕሮግራሞች አስፈጻሚ መ/ቤቶችን አሠራር በዕቅድ መምራት መከታተል ፣ መደገፍ ፣ ማሰልጠን ፣ መገምገምና የተቀናጀ አሰራር የሚኖርበትን የአሰራር ሥርዓት መፍጠር ፣

## 5.2 የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም

### 1. ግብ

የፍትህ ሥርዓቱ በሁሉም የመንግሥት እርከኖች ተሻሽሏል ፡፡

### 2. ዓላማ

2.1 የፍ/ሥ/ማ/ፕሮግራሙን ተግባራዊ ማድረግ የሚያስችሉ ዕቅዶች ተዘጋጅተው ሥራ ላይ መዋላቸውን መከታተልና ተገቢውን ድጋፍ በመስጠት ፈጻሚ ተቋማቱን ማብቃት ፣

- የፕሮግራም ማስፈጸሚያ ሰነድ የሌላቸው ፈጻሚ መ/ቤቶች የንዑስ ፕሮግራም ወይም የፕሮጀክት ማሻሻያ ረቂቅ ሠነዶች እንዲያዘጋጁ እገዛ መስጠት ፣ አፈጻጸማቸውን መከታተልና ማብቃት ፣

- ለ9ኙ የክልሉ ፕሮግራም ፈጻሚ መ/ቤቶች ( ፍ/ቤቶች ፣ ዐቃቢ ህግ ፣ ፖሊስ ፣ማረሚያ ቤት፣ ፍትህ ቢሮ፣ ፀረ-ሙስናና ሥነ-ምግባር፣ ብሔረሰቦች ም/ቤት፣ ክልል ም/ቤት፣ ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት) የዕቅድ አፈጻጸም Check List አዘጋጅቶ መላክና የውይይት መድረክ በመክፈት የጋራ ማድረግ ፣ መከታተልና መደገፍ ማብቃት ማብቃት፣

2.2 የክልል ፍ/ሥ/ማ/ፕሮግራም ፈጻሚ መ/ቤቶችን የዕቅድ አፈጻጸም ሂደት በመደበኛነት በመከታተል ተገቢውን ድጋፍ መስጠት ፣ የተገኙ ውጤቶችን በግብረ- መልስ ማሳወቅ ፣መገምገም ፣ ማብቃትና በራሳቸው ላይ የአሰራር ለውጥ በማምጣት የመልካም አስተዳደር ፖኬጅ ፈጻሚዎች እንዲሆኑ ማስቻል ፣

## ዝርዝር ተግባራት

- በወር 1 ጊዜ በአካል በፈጻሚ መ/ቤቶች በመገኘት በፕሮግራሙ የአፈጻጸም ሂደት ያጋጠሙ ችግሮን ለመፍታትና ተገቢውን ድጋፍ ለመስጠት Check List ማዘጋጀት፣ በCheck List መሠረት የመረጃ ልውውጦችን ማካሄድና ድጋፍ መስጠትና ማብቃት ፣

- የግማሽ ወይም የዓመት የፕሮግራም አፈጻጸም ሪፖርቶችን በመገምገም የተገኙ ውጤቶችን በግብረ- መልስ ማሳወቅና መደገፍ፣

- በክልሉ የፍ/ሥ/ማ/ፕሮግራም አስተባባሪ ኮሚቴ ወርሃዊ መደበኛ ስብሰባ ያለመቋረጥ እንዲካሄድ ቀድሞ አጀንዳዎችን ማሳወቅና ማስታወስ ፣ ስብሰባዎች እንዲካሄዱ ማድረግ ፣ ውሳኔዎችን ለፈጻሚ ተቋማት ማሳወቅና መከታተል ፣ መደገፍ ፣ ማረምና ማብቃት፣

- በፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ አተገባበር በተለይ በፍርድ ቤቶች፣ በአቃቤ ህግ በፖሊስና ማረሚያ ቤቶች የመጣውን ለውጥ ለማወቅ የሚያስችል ትናት በተመረጡ ዞኖችና ወረዳዎች ማድረግ የጥናቱን ውጤትም ለፍትህ አስተባባሪ ኮሚቴው አቅርቦ ማስገምገም፣ ውሳኔዎችን ማሰራጨትና ተግባራዊ እንዲሆኑ መከታተል፣

- የፍርድ ሥርዓት ማሻሻያ ሽፋንን ማሳደግ ፣

- በ1999 የላቀ ውጤት ላስመዘገቡ የወረዳና የዞን የፍትህ አካላት ሽልማት አዘጋጅቶ መስጠት ፣ (ዝርዝሩ በጠቅላይ ፍርድ ቤትና በፍትህ ቢሮ በኩል እንዲቀርብ በማድረግ ፣ በፍትህ ሥ/ማ/ፕ/አስተባባሪ ኮሚቴ ማስጸደቅ) ፣

2.3 በተዋረድ የሚገኙ የመንግሥት እርከኖች ማለትም የዞን፣ የወረዳና የከተማ አስተዳደሮችን የፍ/ሥ/ማ/ፕሮግራም አስተባባሪ ኮሚቴ የዕቅድ አፈጻጸም ውጤት መከታተል ፣ ተገቢውን እገዛና ድጋፍ መስጠትና ማብቃት፣

## ዝርዝር ተግባራት

- ከዞን እስከ ቀበሌ የፍ/ሥ/ማ/ፕሮግራም አስተባባሪ ኮሚቴ ስለመደራጀቱ ክትትል ማድረግ ፣

- የዞን አስተባባሪ ኮሚቴውን ለመደገፍ የሚረዱ ጠቋሚ ዕቅዶችን እና Check List አዘጋጅቶ በመላክ ፣ ውጤቱን መሰብሰብና በግብረ -መልስ ማሳወቅ ፣

- በዞኖች የፕሮግራም አፈጻጸም ፣ በልምድ ለውውጦችና ስልጠናዎች የተገኙ ውጤቶችን ለጥናታዊ ጽሁፍ ዝግጅት በሚያመች መልኩ መረጃዎችን ማሰባሰብና ማጠናከር ፣ ጥናት በማድረግም ማሻሻያ እርምጃ መውሰድና መተግበር፣

- የማወዳደሪያ መስፈርት አዘጋጅቶ የላቀ ውጤት ላስመዘገቡ ሽልማት መስጠት ፣

2.4 የፍ/ሥ/ማ/ፕሮግራም አፈጻጸሙን ከማጎልበት አኳያ በመልካም አስተዳደር ፓኩጅ ትኩረት የተሰጣቸውን ተግባራት አፈጻጸም መከታተልና ተገቢውን ድጋፍ መስጠት ፣

## ዝርዝር ተግባራት

- በክልሉ በወረዳ ዳኝነትና ዐቃቢያነ ህግነት ለሚስማሩ ባለሙያዎች የሚሰጠውን የሙያና የክህሎት ስልጠና አፈጻጸም መከታተልና መደገፍና ማጠንከር ፣

- የኮሚኒቲ ፖሊስንግን ቢያንስ ከ30-50 በመቶ የሚሆኑ ወረዳዎችን እንዲሸፍን ለማድረግ ፈጻሚ ተቋማጽን መደፈግ፣ማሽልጠን ፣መከታተል፣ መገምገምና የልምድ ልውውጥ ማድረግ፣

- ማህበራዊ ፍ/ቤቶችን /ሸንጎዎችን/በአዲስ አሰራርና አደረጃጀት ማጠናከር መከታተልና መደገፍ ፣

- ከወረዳና ቀበሌ ም/ቤት አባላት ምርጫ ጋር የተያያዙ ተግባራትን በሚመለከታቸው አካላት ቅንጅታዊ ሥራ

ተግባራዊ እንዲሆኑ ተገቢውን እገዛ መስጠት ፣ አፈጻጸሙን መከታተል፣

- በየደረጃው ላሉ የሚሊሺያ አባላት በፖሊሲዎች ላይ ሥልጠና ለመስጠት እንዲቻል የክልሉ ሚሊሽያ ጽ/ቤት የሥልጠና ሰነድ እንዲያዘጋጁ መከታተልና የሙያ ድጋፍ መስጠት ፣ ስልጠናውን መደገፍና ማብቃት፣

2.5 በየደረጃው የተቋቋመውን የፍ/ሥ/ማ/ፕሮግራም አስተባባሪ ኮሚቴ አፈጻጸምን የመስክ ሥራ ምልከታ በማካሄድ ወይም የሱፐርቪዥን አገልግሎት በመዘርጋት ማጠናከር ፣

## ዝርዝር ተግባራት

- በክልል ያለው ወደ ዞን. ዞን ወደ ወረዳ ፣ ወረዳና ከተማ አስተዳደሮች ቀበሌዎችን በሞዴልነት መርጦና ተከፋፍሎ በየወሩ እና በዓመቱ መጨረሻ ደግሞ የአፈጻጸም ግምገማ እንዲካሄድ ተገቢውን ደጋፍ መስጠት መከታተልና እርምት መስጠትና መደገፍ ፣

- ለመስክ ሥራ ምልከታ ወይም ለሱፐርቪዥን አገልግሎት የሚውል የማስፈጸሚያ ፕላን በማዘጋጀትና በማጽዳቅ ተገቢውን ድጋፍ ማድረግ ፣

- የተገኘውን የመስክ ሥራ ወይም የሱፐርቪዥን አገልግሎት ውጤት በግብረ-መልስ ማሳወቅና አፈጻጸሙን መከታተል፣

- በተለይ በቀበሌዎች የፍትህ ሥርዓት አስተባባሪ ኮሚቴዎች ከመቋቋም አልፎ ወደ ተግባር በመግባት የተገኘውን ውጤት በመቀመር ተሞክሮ ማለዋወጥ ላይ ትኩረት ማድረግና ማሻሻል ፣ መደገፍ፣ ማሰልጠንና ማብቃት ፣

## 5.3. ያልተማከለ የገጠር ወረዳ አቅም ግንባታ ፕሮግራም

### 1. ግብ

መልካም አስተዳደርን በቀበሌና ወረዳ ለማስፈን በአሰራርና በአደረጃጀት ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል ፡፡

### 2. ዓላማ

#### 2.1 የመልካም አስተዳደር ፓኬጅን በገጠር ወረዳና ቀበሌ መተግበር

- ፓኬጅ በተሟላ ሁኔታ እንዲተገበር ባለቤት ሆኖ የማስተባበር ተግባር ማከናወን ፤
- ከወረዳና ከዞን ወቅታዊ መረጃዎችን በማሰባሰብ በየወሩ ሪፖርት ማቅረብ ፤ ግብረ መልሱን ማሳወቅ ፤ መከታተልና መደገፍ፤
- መልካም አስተዳደር በቀበሌና በወረዳ ተግባራዊ ሆኖ ያመጣውን ለውጥ ለማወቅ የሚያስችል ሰርቬይ ማካሄድ ፤
- ከፌዴራል ተጠናቀው የሚመጡ ጥናቶችን ክልላዊ ቅርጽና ይዘት አስይዞ ተግባራዊ ማድረግ፤

#### 2.2 ያልተማከለ የአካባቢ አስተዳደር በክልሉ እንዲሰርጽ ሥርዓቱ የሚመራበትን ህግ ማውጣትና ተግባራዊ ማድረግ ፤

#### ዝርዝር ተግባራት

- ህጉ በካብኔ እንዲጸድቅ መከታተልና ማስፈጸም
- የጸደቀውን ህግ ማሳተምና ማሰራጨት
- በህጉ ላይ በየደረጃው ሥልጠና መስጠት

- ህጉ በሥራ ላይ መዋሉን ማረጋገጥና መደገፍ

## 2.3 ዝቅተኛ የወረዳ የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃ ጥናትን ማጸደቅ ማሳተም፣ ማሰራጨትና ሥልጠና መስጠት ፣

- ከሚመለከታቸው መ/ቤቶች የቀረበውን እስታንዳርድ በሞዴል በመጠቀም ፣የተጠናውን ሰንድ ማጠናቀቅ፣
- የተጠናውን ሰነድ በማጽደቅ ክልላዊ ዝቅተኛ የአገልግት ደረጃን በየወረዳው መተግበር፣አፈጻጸሙን መከታተልና መደገፍ፣
- ሰነዱን ማሳተምና ማሰራጨት ፣

## 5.4 <u>የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ ፕሮግራም፣</u>

### 1. <u>ግብ</u>

የመንግሥት ተቋማትን የቴክኖሎጂ ተጠቃሚ በማድረግ ሥራን ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ ሁኔታዎች ተመቻችተዋል፡፡

### 2. <u>ዓላማ</u>

በክልሉ የሚገኙ የመንግሥት ተቋማት የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ሆነው ፈጣን ፣ ቀልጣፋና በመረጃ የተደገፈ አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ ፣

### <u>የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት</u>

1. ለ2000 ከፍተኛ ባሙያዎች የመሠረታዊ ኮምፒውተር ስልጠና መስጠት ፣

2. በተለያዩ ዘርፎች ለ100 ባሙያዎችና ኃላፊዎች ስለ ኢኮቴ ሀገራዊ ፖሊሲ ስትራቴጂና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ስልጠና መስጠት ፣

3. በመረጃ መረብ ፣ ኢንተርኔትና በመሳሰሉት ለ500 ባለሙያዎችና ኃላፊዎች ሥልጠና መስጠት ፣

4. ለ250 ባለሙያዎች ( ወረዳ Operators ) ልዩ ልዩ የኮምፒውተርና የመረጃ ሥርዓት ሥልጠናዎችን መስጠት ፣

5. የክልል የICT ማሰልጠኛ ማዕከሉን ማጠናከር በ5 አማካይ ዞኖ መለስተኛ የኢኮቴ ማሰልጠኛ ማዕከል መክፈት ፣

6. ለ34 አዳዲስ ወረዳዎች የወረዳ መረጃ ማዕከል ማቋቋም ፣

7. ለ300 ቀበሌዎች ኮምፒውተር መትከል ፣ ለ6 የተመረጡ ወረዳዎች የማህበረሰብ መረጃ ማዕከል ማቋቋም ፣

8. በየወረዳው የተጓደሉ የICT መሣሪያዎችን ማሟላት ፣

9. የInternet አገልግሎት የማያገኙ ወረዳዎችና ት/ቤቶች አገልግሎቱን እንዲያገኙ ማድረግ ፣

10. በክልሉ የRural Connectivity ሽፋን የሚያድግበትን ሁኔታ ከሚመለከታቸው ፈጻሚ ተቋማት ጋር በመሆን ማመቻቸትና መከታተል ፣

## 5.5 <u>የምህንድስና አቅም ግንባታ ፕሮግራም</u>

### <u>ዝርዝር ተግባራት</u>

- በቢሮው የሥራ ክፍሉን የሚመራና የሚከታተል መዋቅር መዘርጋት፣

- የምህንድስና አቅም ግንባታ ፕሮግራም በፈጻሚ መሥሪያ ቤቶች በተደራጀ ሁኔታ ታቅዶ ተግባራዊ እንዲሆን ማስተባበርና ሙያዉ ድጋፍ መስጠት ፣

- የመከታተያ ቼክሊስት አዘጋጅቶ መከታተልና ግምገማ በማካሄድ ግብረ-መልስ በመስጠት ፕሮግራሙን በክልሉ ውስጥ ተግባራዊ መሆኑን ማረጋገጥ ፣

- ለ2000 በጀት ዓመት ተዘጋጅቶ የጸደቀውን ዕቅድ አፈጻጸም መከታተልና ተገቢውን ሙያዉ ድጋፍ ማድረግ ፣ ስለአፈጻጸሙ ግብረ-መልስ መስጠት፣

  - የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና 5 ቁልፍ ጉዳዮችንና ተግባራትን መከታተል ፣ መደገፍና ማስተባበር ፣

  - የግሉን ክፍለ ኢኮኖሚና የንግድ ሥራ ማስፋፊያ 7 ቁልፍ ጉዳዮችንና 19 ተግባራትን መከታተል ፣

  - የዩኒቨርስቲ የጥራት ቁጥጥር ሪፎርም ተግባራትን ማስተባበር፣ ማቀናጀትና መደገፍ ፣

- ወጣቶች በቴ/ሙያ ትም/ስልጠና ያገኙትን ዕውቀት በመጠቀም በዩኒቨርስቲዎች ግንባታና በገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን እንዲሰማሩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ማስተባበር ፣ አፈጻጸሙን መከታተልና መደገፍ፣

- ሀዋሳ ዩኒቨርስቲ የተጀመረው የCooperative Training በተመረጡ የክልሉ ሌሎች ተቋማትም እንዲጀመር ማስተባበር ፣መከታተልና ማስፈጸም ፣

- የሥራ ክፍሉን የሚመራ ከተለያዩ ፈጻሚ ተቋማት የተውጣጣ አስተባባሪ ኮሚቴ ከግልጽ ኃላፊነትና ተግባር ጋር በማቋቋም ፕሮግራሙን አቀናጅቶ መምራት፣

## 5.6 <u>የሰው ሃይል ልማት ስልጠና</u>

### 5.61. ግብ

በሥራ አፈጻጸሙና በአመለካከቱ ብቃት ያለው የሰው ሃይል ለማፍራት ጥረት ተደርጓል ፡፡

### 5.6.2 ዓላማ

5.6.2.1 የሰው ሃይል ልማት ፕሮግራም መቅረጽ

5.6.2.2 የውጭና የአገር ውስጥ ስልጠናዎችን አማክሎ በመምራት ፍትሀዊ የስልጠና ሥርዓት መዘርጋት ፡፡

5.6.2.3 ከልዩ ልዩ ኮሌጆችና ዩኒቨርስቲዎች ተመርቀው የሚመጡ ምሁራንን የሰው ሃይል ስምሪት ሚዛንን በጠበቀ ሁኔታ እንዲመደቡ ማድረግ ፣

## <u>ዝርዝር ተግባራት</u>

በክልል ፣ በዞን ፣ በወረዳና በቀበሌ ደረጃ የሚገኙ አመራሮችና ባሙያዎች የረጅም ጊዜ የሙያ ስልጠና እንዲያገኙ መደረጉን መከታተል ፣

1. በርቀት ትምህርት ከዲፕሎማ ወደ መጀመሪያ ዲግሪ 750 በመጀመሪያ ዲግሪ ፕግራም ትምህርት ማስጀመር ፣

2. ከመጀመሪያ ዲግሪ ወደ ሁለተኛ ዲግሪ 120 አመራሮች እንዲሰለጥኑ ማመቻቸት ፣
    - ከክልል በርቀት ትምህርት 20 በማስተርስ ዲግሪ
    - ከክልል በመደበኛ ትምህርት 5 በማስተርስ ዲግሪ
    - ከዞን በመደበኛ ትምህርት 5 በማስተርስ ዲግሪ

- ከዞንና ወረዳ በርቀት ትምህርት 90 ባለሙያና ኃላፊ በማስተርስ ዲግሪ እንዲሰለጥኑ ማድረግ

3. ከአገር ውስጥና ከውጭ አገር ዩኒቨርቲዎች ለሁለተኛ ዲግሪ በሚሰጥ የትምህርት ዕድል ብቃት ያላቸው ባለሙያዎች ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ተወዳድረው የዕድሉ ተጠቃሚ እንደሆኑ ማድረግ ፣

## 5.7 የፐብሊክ ሴክተር አቅም ግንባታ ፕሮግራምን መተግበር

### 5.7.1 ግብ

የፐብሊክ ሴክተር አቅም ግንባታ ፕሮግራሞች (PSCAP) ዕቅድ በ2000 ዓ/ም ተግባራዊ ሆነዋል ፡፡

### 5.7.2 ዓላማ

5.7.2.1 የክልሉ የፐብሊክ ሴክተር አቅም ግንባታ ፕሮግራም (PSCAP ) ንዑሳን ፕሮግራሞች በዕቅድ የተያዙ ልዩ ልዩ ስልጠናዎች መስጠት ፣

## ዝርዝር ተግባራት

- ፈጻሚ መ/ቤቶች ዓመታዊ ዕቅዳቸውን አዘጋጅተው እንዲያቀርቡ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ፣

- በድርጊት መርሀ-ግብሩ መሠረት ተፈጻሚ መ/ቤቶች የሚቀርቡ የስልጠና TOR ሥራዎችን ማረጋገጥ ፣

- የዓለም ባንክን የይሁንታ ምላሽ / No objection / የሚጠይቁ የሥልጠና ዓይነቶችን ለባንኩ ልኮ ምላሽ በመቀበል ውጤቱን ለፈጻሚዎች ማሳወቅና ስልጠናውን መከታተል ፣

- በክልሉ ስልጣን ደረጃ የሚከናወኑ ስልጠናዎች በቀረቡት ዝክረ ሀሳቦች (TOR) መሠረት ስልጠናውን ማካሄድ ፣ የስልጠናውን አሰጣጥ መገምገምና የስልጠናውን አፈጻጸም ሪፖርት ማዘጋጀት፣

5.7.2.2 በክልሉ የፐብሊክ ሴክተር አቅም ግንባታ ፕሮግራም (PSCAP) ንዑሳን ፕሮግራሞች በዕቅድ የተያዙ ልዩ ልዩ ግዥዎችን መፈጸም ፣

**<u>ዝርዝር ተግባራት</u>**

- በድርጊት መርሀ ግብሩ መሠረት ከፈጻሚ መ/ቤቶች የሚቀርቡ የዕቃ ግዥ ዝክረ ሀሳቦች (TOR) ማረጋገጥ ፣
- በአገር አቀፍና በአካባቢ /NCB, ICB, LS/ ለሚገዙ እቃዎች የግዥ ሰነድ በማዘጋጀት በግዥ መመሪያው መሠረት ግዥዎችን መፈጸም ፣
- የግዥ አፈጻጸም ሪፖርት ማዘጋጀት ፣

5.7.2.3 በክልሉ የፐብሊክ ሴክተር አቅም ግንባታ ፕሮግራም (PSCAP) ንዑሳን ፕሮግራሞች በዕቅድ የተያዙ ልዩ ልዩ የአማካሪ ግዥ መፈጸም ፣ ( በራስ አቅም ማከናወን)

**<u>ዝርዝር ተግባራት</u>**

- በድርጊት መርሀ ግብሩ መሠረት ከፈጻሚ መ/ቤቶች የሚቀርቡ በራስ ሃይል የሚሰሩ ወይም የአማካሪ የግዥ ዝክረ ሀሳቦች (TOR) ማረጋገጥ ፣

- የአማካሪዎችን ፍላጎት ማረጋገጫ በመያዝ ለሚወጡ ጨረታዎች የሚወዳደሩትን ለይቶ መያዝ / Short list / ( ከራስ አቅም በላይ መሆኑ ተረጋግጦ) ፣

- ከፈጻሚዎች ከቀረበው ዝክረ ሀሳብ (TOR) መሠረት የአማካሪ ግዥ ወይም በራስ ሀይል ለመስራት ሰነድ በማዘጋት ለዓለም ባንክ መላክ ፣

- በተጠየቀው መሠረት No objection ምላሽ ሲመጣ የጨረታ ሂደቱን ወይም በራስ ሃይል የመስራት ሂደትን መፈጸም ፣

- ፈጻሚዎች በውለታው መሠረት የአማካሪ ስራውን ለማሰራታቸው መከታተል ፣

- የአማካሪ ግዥውን አፈጻጸም ሪፖርት ማዘጋጀት ፣

## 5.8. የሴቶችን ተጠቃሚነት በአመራር ቦታዎች ፣ በሲቪል ሰርቪሱ የሥራ መደቦችና በስልጠና በልዩ ሁኔታ በማረጋገጥ ድጋፍ ማድረግ ፣

### 5.8.1. ግብ

ሴቶች በአመራር ቦታና በስልጠና ተገቢ ድርሻቸውን አግኝተዋል፡፡

### 5.8.2. ዓላማ

1. ሴቶች በሲቪል ሰርቪስ የሥራ መደቦች ያላቸው ድርሻ አሁን ካለበት በ10% እንዲያድግ ማድረግ ፡፡

2. በሲቪል ሰርቪስ አመራር ቦታ ያላቸውን ድርሻ ለማሳደግ ልዩ ልዩ የድጋፍ እርምጃዎችን መውሰድ ፣

## ዝርዝር ተግባራት

- በደረጃ እድገት በቅጥር ጊዜ ለሴቶች የሚሰጠው ተጨማሪ ነጥብ በየደረጃው ሳይሸራረፍ እንዲቀጥል ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ፣
- በሲቪል ሰርቪስ የሥራ መደቦች ላይ የሴቶች ድርሻ ከፍ እንዲል መመሪያ ማዘጋት አፈጻጸሙን መከታተልና መደገፍ ፣
- ሴቶች በአመራር ቦታዎች በተገቢው እንዲመደቡ ልዩ ልዩ ድጋር ማድረግና በቁርጠኝነት መፈጸም ማስፈጸም ፣